# ስለ አማርኛ ፊደል መሻሻል የተደረጉ ጥናቶች መዘርዝር

ስለ ፊደል መሻሻል ጥናቶች ዘገባ ከመግባቴ በፊት ፊደል ምን ማለት እንደሆነ መግለጹ አስፈላጊ ስለሆነ ከሊቁ የቀረበውን ማቅረቡ በቂ ግንዛቤን ያስጨብጣል። ፊደል ማለት ይላሉ ሊቁ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የነገር የቃል ምልክት አምሳል ወይም መግለጫ ማስታወቂያ ማለት ነው ሥዕል እንደ ማለት ነው[1]። ይህን ያማርኛ የቃል ምልክት ህግ እንዲጠብቅና ሕገ ወጥ የሆኑትም ሕግ እንዲጠብቁ ባጠቃላይ ፊደላችን ይዘት ጥበቅ እንዲሆን ጥናት እና ምርምር ከተጀመረ አንድ ዘመን እንኳን አልሞላውም። ነገር ግን አማርኛ ቋንቋ ልሳነ ነገስት ከተሰኘበት ከዛጉዌ ዘመነ መንግስት ወይም ከይኩኖ አምላክ አንድ ወይም ሁለት ዘመን ቀደም ብሎ የመጀመሪያው ያማርኛ መሸሻል የተደረገበት መሆኑ ታሪኩ ምስክር ነው። ይህም ማለት በግዕዙ ውስጥ የሌሉ አዳዲስ ምልክቶች የተፈጠሩበት ጊዜ ነው። ላማርኛ ቋንቋ ለፊደሉና ለቃሉ አባቱና እናቱ ሰፌዱ ወንፊቱ ግእዝ መሆኑ የማያጠያይቅ ቢሆንም ላማርኛ ሙሉዕ አልነበረም።

አማርኛ የግዕዙን ፊደል እንዳለ ወስዶ የራሱን ማለት ግዕዙ የሌሉትን በተልምዶ አነጋገር ያማርኛ ዲቃሎች የሚባሉትን( ጀ ዠ ጨ ኸ ኘ ሸ ቸ) ፈጥሮ እስከ አሁን ይሰራበታል። ማን እንደፈጠረው ወይም ጣፈው ማንነቱ ባይታወቅም ያው ከቀሳውስቱ ወገን መሆኑ አያጠራጥርም። ይህ ከሆነ ከዘመናት በኋላ አጼ ሚኒሊክ ባንድ ክረምት አንኮበር ወርደው ከተማውን በሚያድሱበት ጊዜ አዲስ ፊደል መፈደላቸውን ሟቹ ዶ/ር አብርሀም ደሞዝ[2] ባሳተሙት መጣጥፋቸው ሲጠቁሙ። ሚኒሊክ መሆናቸው እና በምን ምክንያት የፊደሉ መሻሻል እንዳስፈለገ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን አመልክተዋል። አያይዘውም መሸሻ ወርቄ ፈጥሮት ሚኒሊክ በስማቸው አሳውቀውታል ይላል። የታሪኩን ምርምር ለታሪክ ሊቃውንት ትቼ ወደ ጉዳዩ ልግባ።

የሚኒሊክን የማሻሻል ፈለግ ተከትሎ አልፎ አልፎ ውይይት ይደረግ እና ጉዳዩ ይነሳ እንደነበር ቀደም ባሉት በአእምሮ እና በብርሀንና ሰላም ጋዜጦች ይወጣ ነበር። ትኩረቱም የተንዛዛውን ፊደል በተለይ ከግዕዝ የተወረሰውን ላምርኛ ጥቅም የማሰጡትን ወይም ልዩነት የሌላቸውን መቀነስ እንደሚያስፈልግ እና አዲስ ምልክቶችን መጠቀም የሚል ነበር። በዚያን ጊዜ ከታወቁት ሊቃውንት አንዱ የነበሩት አባ ተ/ማሪያም ሰምሃራይ [3] የተባሉት ይጠቀሳሉ። የምዕራቡን ዕውቀት እና ያገራችንንም ትውፊቱ ጠንቅቀው ያወቁ በመሆኑ ለደጊም እና ለሳድስ ምልክቶችን በመጠቀም መጽሐፍ ማተማቸው ይታወቃል። የሳቸውን የመሰለ ተመሳሳይ ስራ የተጠቀሙት ሀዲስ ዓለማየሁ ከብዙ አስርታት በኋላ አቅርበው የተጠቀመበት አልነበረም[4]። ጠንከር ያለ ግፊት የመጣው የመኪና መጻፊያ አገራችን በገባበት በ፳ኛው ክ/ዘመን መባቻ ግድም ነው። ለዚህም ማሻሻያውን በሚመለከት ከጠላት ወረራ በፊት የቀረቡት ጥናቶች የሚከተሉት ቀርበዋል፡-

፩/ በ፲፱፻፲፪ዓ/ም አቶ ዓለሙ ሀ/ሚካኤል በአማርኛ ፊደል አንድ የጽሕፈት መኪና አሰናድተው አቅርበው ንጉሡ ነገሥቱ ቀ/ኀ/ሥ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ዘመን ይጠቀሙበት እንደነበር ተገልጿል።

፪/ አቶ አያና ብሩ[5] በ፲፱፻፳፫ዓ/ም አንደ ያማርኛ የጽሕፈት መኪና አዘጋጅተው በስራ ላይ እንዲውል ማቅረባቸው ይነገራል።

፫/ ዶ/ር ዓለመ ወርቅ[6] በዚሁ በ፲፱፻፳፫ዓ/ም የአማርኛ የጽሕፈት መኪና እንግሊዝ አገር አሰርተው ማቅረባቸው ይታወቃል።

፬/ ሊቁ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ለጽሕፈት መኪና ላማርኛም ለግዕዙም ሊያገለግሉ የሚችሉትን ፊደላት ሰብስበው ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው አሳትመው አቅርበው ነበር።

፭/ የተከበሩ አቶ አበበ ረታ[7] በመምህርነት ባገለገሉበት ጊዜ ያማርኛ ፊደል ለህጻናትና ላልተማሩ አዋቂዎች እንዳያስቸግር ቀናና ቀልጣፋ በሆነ ዘዴ በሁለት ዐይነት መንገድ የተሰራ ጥናት በ ዓ/ም ለትምህርት ሚ/ር አቅርበው በስራ ላይ ሳይውል መቅረቱ ተመዝግቧል። ይህም የጥፈት መኪናውን ችግር ለማቃለል ሳይሆን ለተማሪና ላስተማሪ ስራውን ለማቅለል ነው።

ሶስት ዓይነት የማሻሻያ ዘዴዎች ከዚህ በታች ይቀርባሉ እነሱም የልዑል ራስ እምሩ አንዱ ሲሆን ሁለቱ የአቶ አበበ ረታ ናቸው።

**የልዑል ራስ እምሩ የማሻሻያ ዘዴ**

ይህ ማሻሻያ ራስ እምሩ ያቀረቡት ሲሆን አካሄዱም በ    ዘይብሎች[8] እና ስድስት ድምጽ ሰጪ አዕጹቅ[9] ፊደላት ናቸው።

የዚህ ማሻሻያ አካሄድ የሚከተሉት ባህርያት ወይም ፀባይ አለው

፩፡ ምልክቶችን ሁላ ትቶ በአ ድምፅ ሰጪነት ይሠራል

፪፡ በአራት ፊደል ይጻፍ የነበረውን በስምንት ስለሚጽፍ እጥፍ ጊዜ ይወስዳል

**የአቶ አበበ ረታ የማሻሻያ ዘዴ**

የአቶ አበበ ረታ ማሻሻያ ሁለት ዓይነት መንገድ ወይም አካሄድ አለው።

አንደኛ አካሄድ የተባለው በ    ዘይብሎችና በስድስት ድምፅ ሰጪ ፊደላት የተዘጋጀ ነው። እነዚህ ግዕዝ ፊደላት በንባብ ጊዜ የግዕዝ ድምጻቸውን ትተው በሳድስነት እንዲነበቡ የተደረጉ ሲሆኑ በግዕዙ በተ ደንብ በተነገረ ጊዜ ኸአ በሚያሰኝ ድምፅ እንዲነበቡ የተደረጉ ናቸው፡፤ ጠብቆ የሚነበብ ቃል ሲኖር ፊደሉ በደጊም እንዲጻፍ ሆኗል።

የዚህ ማሻሻያ አካሄድ የሚከተሉት ባህርያት ወይም ፀባይ አለው

፩፡ በአ ቤት ድምፅ ሰጪነት ይሰራል

፪፡ የግዕዝ ድምፅ ቀርቶ ግዕዙ በሳድስ ድምፅ ይሰራል

፫፡ እጥፍ ጊዜና እጥፍ ጉልበት ይጠይቃል

፬፡ በአማርኛ ጽሕፈት አብዛኛዎቹ የሳድስ ፊደላት መሆናቸውን ይገልጻል

ሁለተኛ አካሄድ የተባለው ላማራጭ የቀረበ ሲሆን እሱም በ    ዘይብሎችና በስድስት ድምፅ ሰጭ ምልክቶች የተዘጋጀ ነው። ግዕዝ ግዕዞቹ ምንም ምልክት ሳይታከልባቸው የግዕዝ ድምጻቸውን እንደያዙ ይቆያሉ። "ሀ. አ". ከላይ እንደተገለጸው "ኸ. አ" በሚያሰኝ ድምፅ ይነገራሉ። የሚጠብቁ ቃላት ሲያጋጥሙ በደጊም ይጻፋሉ። የሳድስ እና የሳብዕ ምልክቶች በፊደሉ በስተቀኝ ሲውሉ፤ የካዕብ፣ የሳልስ፣ የሐምስና የራብዕ ምልክቶች ከፊደሉ በስተግራ ይውላሉ። ምልክቶች የተባሉት ፊደላቱ ሁሉ ይቀበሏቸዋል የተባሉት ተመርጠው ነው። አረቢ የሚባሉት በራስ ቀጸላ ምልክት (-) ይለያሉ። ከነዚህም ውስጥ ከዡና ከጨ በስተቀር ሌሎቹ መልካቸው አይለወጥም። አራቱ ፍንጽቅ ፍፊደላት[10] ተመሳሳያቸው ከሆኑት ከ ሀ፣ ቀ፣ ከ፣ እና ገ ላይ ወ እየተጨመረ ይነበባሉ።

የዚህ ማሻሻያ አካሄድ የሚከተሉት ባህርያት ወይም ፀባይ አለው

፩፡ ያማርኛን ፊደሎ ብዛት ያሳጥራል

፪፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የፊደል አናጋሪነት ቀርቶ የምልክት አናጋሪነት ተፈጥሯል

፫፡ ለሚጠብቁ ቃላት ሕግ ይወጣላቸዋል

፬፡ ፍንጽቅ ፊደላት በወ እርዳታ መልካቸውን ይቀይራሉ

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዶ/ር ሉባከ የተባሉ አሜሪካዊ አኢትዮጵያን በጎበኙበት ሰአት ፊደልን ለማሻሻል የተመሰረተው ኮሚቴ ስራውን ሲያካሂድ በጊዜው በመገኘታቸው ከራብዕና ከሳድስ ጭረት በስተቀር ካቶ አበበ ረታ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ አቅርበው ነበር። የዚህ አካሄድ በ ዘይብሎችና በስድስት ድምፅ ሰጪ ምልክቶች የተዘጋጀ ነው። ዘይብሎቹ የሆኑት ፍንጽቅ ፊደላት ተጨምረው ነው። አዕጹቅ ፊደላት ምልክቶች በሙሉ በስተግራ ሲውሉ፤ ራብዕ፣ የቅናት ምልክት ሲኖረው ሳድስ ደሞ የድፋት አለው።

የዚህ ማሻሻያ አካሄድ የሚከተሉት ባህርያት ወይም ፀባይ አለው

፩፡ የፊደሎችን ብዛት ያስጥራል

፪፡ አናባቢዎች እንደ አምስተኛው ሐ አካሄድ ምልክቶች ይይዛሉ

፫፡ የራብዕና የሳድስ ምልክቶች የቅናት ምልክቶች በመሆናቸው

ካማርኛ ፊደል ጋር መልክም ወገናዊነትም የላቸውም።

፬፡ የዚህ አካሄድ ፊደሎች በአምስተኛው ሐ ከተነገረው አካሄድ የበዙ ናቸው።

እነኚህ እንድግዲህ ከጠላት ወረራ በፊት የተደረጉ ጥናቶች ናቸው ከወረራው በኋላ የመጀመሪያው የለውጡን ማዕበል የቀሰቀሰው ያቶ ዘውዴ ገ/መድኅን ነው።

**የአቶ ዘውዴ ገብረ መድኅን የማሻሻታ ዘዴ**

አቶ ዘውዴ ገ/መድኅን በ ዓ/ም በአዲስ ሥርዓት የተዘጋጀ ፊደል በሚል አርዕስት ያቀረቡት ማሻሻያ በ ዘይብሎችና በሰድስት ድምፅ ሰጪዎች ወይም አናባቢዎች የተዘጋጀ ነው። የካብዕ፣ የሳልስ. የሐምስና የሳብዕ ምልክቶች ከፊደሉ በስተግራ ሲውሉ የሳድስ ምልክይ ከፊደሉ በስተቀኝ ይውላል። የራብዕ ደሞ በስተቀኝ ግርጌ እግር ተፈጥሮለታል።

የዚህ ማሻሻያ አካሄድ የሚከተሉት ባህርያት ወይም ፀባይ አለው

፩፡ ያማርኛ ፊደሎች ብዛት ያጥራል

፪፡ አናባቢዎች ምልክቶች ናቸው

፫፡ የካብዕ፣ የሳልስ፣ የሐምስና የሳብዕ ምልክቶች በስተግራ ይጣፋሉ

፬፡ የሳድስ ምልክት በስተቀኝ ይጣፋል

፭፡ የራብዕ ምልክት በስተቀኝ ግርጌ እግር ይውላል

ይህ ጽሑፍ ከወጣ በኋላ የፊደል መሻሻል ነገር ጉዳዩ ከሚከነክናቸው ጥቂት ሊቃውንት አልፎ ብሔራዊ ጉዳይ በመሆን የጽሕፈት ሚኒስትሩ አስፈላጊው ጥናት እንዲደረግና እንዲቀርብ ባዘዘው መሰረት የሚከተሉት አምስት ስብሰባዎች ተደርገው ከብዙ ክርክር በኋላ ውሳኔ ላይ ደርሰው ኮሚቴው ስራውን በሚገባ አከናውኖ ተበትኗል። ዝርዝሩ ይኼው።

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት አንድ ሌላ ጠቢብ ዶ/ር እንግዳ የተባሉ የተፈሪ መኮንን ት/ቤት የብላታ መርስኤ

ጎ/ወ/ቂ ተማሪ የነበሩ ያማርኛ ፊደል ከነጓዙ ከነአበጋዙ ማለት ስላሳ ሶስቱ በስድስት መደብ እና አራቱ አረቢዎች ማለት ሏ፣ ሟ ባምስት መደብ ተጠቃለው በድምሩ ወደ እንደሚደርስ እና የፈረንጁ ግን በ ሳይበልጥ ብዙ እንዲሚሰራበት ካስረዱ በኋላ የኛም ፊደል በዚሁ ዐይነት ቢወሰን ጠቃሚ መሆኑን ገልጸውላቸው ነበር። ብላታም የግዕዙ ፊደል የታሪክ ቅርስና ኩራት ስለሆነ ሳይነካ እንዳለ እንዲሰራ ለሌላ ማገኛውም ዘመናዊ ስራ ግን የላቲኑን በመጨመር እንዲሰራበት በ ዓ/ም ለት/ሚኒስትሩ ለብላቴን ጌታ ኅህሌ ጸዳሉ አቅርበውት እንደነበር ይታወቃል። ይህ ጉዳይ እንደገና በ ዓ/ም የፊደል መሻሻል ጉዳይ ሲነሳ በድጋሚ ተነስቷል።

ኪሚቴው እንዲሻሻል የፈለገው ፊደል ፍሬ ሀሳብ በድርሞ ለማቅረብ ይህ ነው። የግ ዕዝ ፊደሎች ቀደም ብለው በልዩ ልዩ ደምፅና አገባብ ያገለግሉ የነበሩትን አምስት ፊደላት ማለት ሐመሩ ሐ፣ ንጉሠ ሠ፣ ብዙኃኑ ኃ፣ ዐይኑ ዐና ፀሐዩ ፀ ላማርኛ ልዩ ድምጽ ስለለላቸው ለማገኛውም ዐ ድምፅ ዐይኑ ዐ ለማገኛው ፀ ድምፅ ሳድቁ ጸ እንዲሰራ። እንዲሁም ደግሞ ተደራራቢ ፊደሎችን በመጥራት አዲስ ፊደል የሆኑት አረቢዎች ማለተ ቧ፣ ሟ ቀርተው ይህን ዐይነት ጽሕፈት ቢገኝ ጥዋ፣ ምዋ እየተባለ እንዲጻፍ ነው። የነኚህ ፊደሎች መቅረት ሸክምና ጥናትን ከማቅለል በስተቀር የሚያጎሉት ነገር አለመኖሩን ቢኖር ጥናት ማብዛትና ጊዜ መፍጀት ብቻ መሆኑን ነው። አሁን ወደ ኪሚቴው በስበሰባ የተከራከረባቸውን ጉዳዮች ዝርዝር እንይ።

## አንደኛው ስብሰባ

ከምር ያማርኛን ፊደል ለማሻሻል የተደረገ ጥረት/ጥናት የቀረበው በ ዓ/ም 'ለወጣቶች ዕድል ከትምህርት ወዳጆች' በሚል አርዕስት አንድ ጽሑፍ ከታተመ በኋላ ነው። አሳታሚዎቹም የትህምርት ወዳጆች በመባል የሚጠሩት ራስ እምሩ፣ አቶ አበበ ረታ እና ብላታ መርስኤ ሀዘን ወ/ቂርቆስ[11] ናቸው። ዶ/ር ሉባክ የሚባል አሜሪካዊ የስነ ትምህርት ጠበብት በወቅቱ ኢትዮጵያን ሊጎበኝ መጥቶ ስለነበር በስብሰባው ተገኝቶ አስተዋጽኦ ማድረጉ ይታወቃል። የመሻሻሉን ማዕበል ያስነሳው ግን ከላይ የተጠቀሰው የአቶ ዘውዴ ገ/መድኅን በ ዓ/ም በአዲስ ሥርዓት የተዘጋጀ ፊደል በሚል ርዕስ የፊደልን መሻሻል የሚጠቁም ጽሁፍ በቀረበበት ጊዜ ነበር።

ከንጉሠ ነገሥቱ መንግስት የጽሕፈት ሚኒስቴር መጋቢት ቀን ዓ/ም ይህ ባዲስ ሥነ ሥራት የተዘጋጀው ፊደል ጉዳይ አስፈላጊው ጥናት ተደርጎ እንዲቀርብ በታዘዘው መሰረት የመጀመሪያው ስብሰባ ሚያዚያ ፬ ቀን ዓ/ም ባቶ አበበ ረታ ሰብሳቢነት የተከበሩ አቶ አዲስ ዓለማየሁ፣ ብላታ መ/ሀ/ወ/ቂርቆስ፣ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ፣ አቶ ስይፉ ፈለቀ ባሉበት ጽሑፉን ያዘጋጁት አቶ ዘውዴ ከሚኒስቴሩ ተወከለው ባስረጂነት ቀርበው ውይይቱ ተጀመረ። ስብሳቢው ውውይቱን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ይህን ባዲስ ሥራት የተዘጋጀ ፊደል ኮሚቴው ሀሳብ እንዲያቀርብበት ከጽሕፈት ሚኒስትሩ መታዘዙን ከገልጹ በኋላ ከ አመት በፊት ተመሳሳይ የሆነ ጥናት ተደርጎ አንዳንድ የቤተ ክህነት ሰዎች አገርን ባህልን እና ሀይማኖትን የሚነካ ነገር ነው በማለት ስለነቀፉት እና ስለተቃወሙት ጥናቱ የትም ሳይደርስ መቅረቱን ታሪኩን በድርሞ በማቅረብ ውይይቱን ከፈቱ።

በመጀመሪያ ብላታ መ/ሀ/ወ/ቂ የፊደሎችን ብዛት ለመቀነስ ልጆችም በፍጥነት ለማጥናት እንዲችሉ ለማድረግ ጉዳዩ ሲጠና ቆይቶ በምልክቶች ላይ ለውጥ እንዲደረግ የጦፈ ሀሳብ እንደነበር ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በፍጹም ስላልተቀበለችው ጉዳዩ ማሰሪያ ሳገኝ መቅረቱን ካብራሩ በኋላ ፊደልም የቤተ ክርስቲያን ልዩ የግል ንብረት መሆኑን ጠቅሰው ከቤተ ክህነት አንድ አባል ተጋብዞ ከኮሚቴው ጋር በጥናቱ እንዲሳተፍ የሚል ሀሳብ አቀረቡ። ሀዲስ ዓለማየሁ ደሞ የቤተ ክርስቲያን የግል ንብረት ነው ከተባለ እና እስራ ላይ የማይውል ከሆነና ድምጽን በድምጽ የመሻር ሀይል ቤ/ክርስቲያን ካላት ጊዜአችንን ባናጠፋ ጥሩ ነው። ነገር ግን ጉዳዩ በድምጽ ብልጫ የሚወሰን ከሆነ ከቤተ ክህነት አንድ ሰው ተጋብዞ ጥናቱ ይቀጥል ብለው ሀሳብ ሰጡ።

የተከበሩ አቶ ሚሊዎን ነቅንቅ ደሞ የቤ/ክ የግል ንብረት ነው የሚለውን ተቃውመው ጉዳዩ የመንግስት እና የህዝብ እንጂ የቤ/ክ የግል ንበረት ከሆነ ግብር ክፈሉ ልንባል ነው ካሉ በኋላ አያይዘው ከቤ/ክ አንድ አባል ተጋብዞ አብሮ እንዲያጠና ደግፈው ቤ/ክ ድምጽን በድምጽ የመሻር ሙብት እንደሌለው በማመን መሆኑም አዝገነዘቡ። ቀጥለውም የፊደል መሻሻል ጉዳይ አዲስ ነገር እንዳልሆነና ከ አመት በፊትም ጥናቱ መካሄዱን ካዛሬው ጋር ልዩነት ካለው የመታረቂያ ነጥብ እንደማይጠፋ እና በውጤቱ ከተስማማን እስራ ላይ የማዋሉ ጉዳይ ሀሳብ እንድሰጥ ከተፈቀደልኝ መንግስት ባዋጅ እና በህግ ካላጸደቀው ፊደል የህዝብ ንብረት መሆኑ ካልታወቀና ካልተረጋገጠ እንዲያው ፊደል በዚህ መንገድ ይሻሻል በማለት ብቻ ጥናታችን ግቡን ይመታል ብሎ

ማመን አዳጋች መሆኑን ገልጸው በመጨረሻ ህጉና ደንቡ ከወጣ በኋላ ሁለት ዐይነት ፊደሎች እንደሚኖሩ ሲያብራሩ አንዱ ህግን እንዲጠብቅ የተደረገው ፊደል ለመንግስት መ/ቤቶች እና የግል ድርጅቶች መሥሪያ ሲሆን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የማተሚያ ቤቶች የሚታትሙትን ሁሉ በዚህ ህግን በጠበቀው ፊደል እንዲሆን ይታዘዛል። ሁለተኛው ግዕዝ ጥንታዊ ቋንቋ ስለሆነ በግዕዝ ቋንቋ የሚታተሙ ሁሉ በዚሁ በግዕዙ እንዲታተሙ የሚያዝ ይሆናል ብለው ሀሳባቸውን አቀረቡ።

በዚሁ ላይ የተከበሩ አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ ሁለት ዐይነት ፊደል የሚለው ብዙ የምጣኔ ሀብት ወጪ ስለሚያከትል ለሁሉም ቋንቋዎች ሥርዐትን የጠበቀው ፊደል መስራት አለመስራቱን ጥናት ሊሰረግበት ያስፈልጋል በማለት ሀሳብ አቀረቡ። ቀጥለው አቶ ዘውዴ ገ/መ የፊደሎችን ምልክት አንድ ዐይነት እንዲሆኑና እንዲያጥሩ ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያብራሩ አማርኛን ለአሜሪካኖች ሲይሥተምሩ የፊደላቱ ህገ ወጥነት ብዛት አንዱን ከሌላው ለመለየት እንዳስቸገራቸው እና ኋላ ምልክቶቹን ባንድ ዐይነት ስርዐት አስይዘው ሲያስተምሯቸው እንዴት በቶሎ መማር እንደቻሉ እንደተረዱ ገለጹ። ቀጥለውም የፊደሎች ማነስ ለመኪና ጽሕፈትም ሆነ ለዕለት ከለት ስራ በፍጥነት እንዲቀላጠፍ ከማስቻሉም በላይ ፊደላችን ህግና ስርዐት ካስያዝነው ፊደል የሌላቸው ያፍሪቃ አገሮች ባማርኛ ፊደል ሊጠቀሙ ማሰባቸውን ገልጸው ሥራት መጠበቁ ከፈ ያለ ጥቅምና ስም እንደሚያስገኝ አብራሩ።

ቀጥለው ብላታ መ/ሀ/ወ/ቂ ከ    አመት በፊት የተደረገው ጥናት አና ባቶ ዘውዴ የቀረበው ተመሳሳይ እንደሆነና ልዩነቱ ራብዑ ላይ ብቻ እንደሆነ ይኼውም ያቶ አበበ ረታ የራብዑ ፊደል የተሰጠው ቅጥል እንደ ጥንታዊው ልማድ መሰረት ከ “ታ” ተመሳሳይ ሲሆን ራቡን በሙሉ በዚሁ መንገድ እንዲሄድ አድርገዋል። ያቶ ዘውዴ ግን ቅጥሎችን በቀኝ ግርጌ ወደታች እንዲሆን ማድረጉ እንጂ የቀረው አንድ ዓይነት መሆኑም በጥያቄ ካረጋገጡ በኋላ አቶ ዘውዴን ለግርማዊነታቸው ያቀረበው በህግ እንዲወጣ ነወይ ብለው ጠይቀውት እሱም በህግ ወይም ባዋጅ ሳይሆን ህዝብ እንዲያውቀው ተደርጎ በጊዜ ብዛት በተሻሻለው ፊደል እንዲሰራበት ነው ብለው መልስ ሰጡ።

አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ካ    አመት በፊት ተደርጎ የነበረው ጥናት ፍጹም ተረስቶና ተድበስብሶ መቅረቱን ግልባጩ በደራሲዎች እንጅ እንኳን እንዳልተገኘ በት/ሚ ግምጃ ቤት ፈልገው እንዲያገኙ በኮሚቴው መታዘዛቸውን ገልጸው፡፤ ጥናቱ ከተገኘ በስራ ላይ የሚውልበት መንገድ ወይም ድርጅት ካልተዘጋጀለት ባክኖ ይቀራል ህግ ይውጣ የሚለውን ሀሳብም ያቀረብኩት እንዳለፈ ተድበስብሶ እንዳይቀር ነው። ካሉ በኋላ አስከትለው እንቅፋት ባይጠፋም እንቅፋቱ ከሚያስከትለው ጉዳት የኢትዮጵያ ጥቅም ስለሚበልጥ ጉዳዩ ሊታሰብበት ይገባል ካሉ በኋላ በህግ ይውጣ ሲባል ድንገተኛ ሳይሆን ረዘም ያለ የመለማመጃ የመሰናጃ ጊዜ ያስፈልጋል። ማንበብና መጻፍ የሚችል ግን ህግ የተከተለውን ፊደል ለመማር ካስር ደቂቃ በላይ አይፈጅበትም ምክንያቱም የሚያጠናው ስድስቱን ምልክቶች ብቻ ነው። ማተሚያ ቤቶች ባዲሱ ዘዴ እንዲሰሩ ለማድረግ ግን አንድ አመት ያህል ያስፈልጋል ብለው አብራሩ። አቶ ሰይፉ ደሞ አሁን የሚጠናው የፊደል ጉዳይ በስራ ላይ የሚውልበት መንገድ ካልተገኘ ጥናቱ ዋጋ ያጣል ካሉ በኋላ በየመስሪያ ቤቱ ህግ የጠበቀው እና የድሮውን ጎን ለጎን እንዲሰራበት ቢደረግ ከጊዜ ብዛት አዲሱ አሮጌውን ሊያስለቅቀው ይችላል ሲሉ ህሳባቸውን ሰጡ። አቶ ዘውዴ ይህን ባዲስ ስርዐት የተዘጋጀውን ፊደል ያዩት ሁሳ ሊቀበሉት ፈቃደኛ መሆናቸውን ብዙ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች ቀናና ቀልጣፋ በመሆኑ በደስታ የተቀበሉት መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ አበበ ረታ አቶ ዘውዴ ስላቀረቡት ምልክት በራብዑ ቅጥል ላይ በኛ ፊደል የፊደሎች እግር አቀማመጥ ከመስመር እንደማያልፍ ከመስመር በታች የሚውል እንደሌለ የሳቸው ከዚህ እንደማይለይ አስረድተው አቶ ዘውዴም ከመስመር በታች የሚውል ፊደል እንደሌለ እና ያቀረቡትም ሀሳብ ለማማረጫ እንዲሆን እንጂ እሱ ይጽና ለማለት እንዳልሆነ ዶ/ር ሉባክ እንደገለጹት ቀልጣፋና ያገርን እና የፊደልን ወግ የያዘው እንዲወሰድ እንዲረዳ ነው በማለት አስረዱ። ቀጥለው ሰብሳቢው አቶ አበበ ረታ አዲሱን ፊደል የተቀብልን እንደሆን የተማሪን የመማሪያ ጊዜ ያሳጥራል የላቲን ይጨመር ካልን ረጂም ጊዜ ይወስዳል የተማረውንም ያልተማረ ያደርጋል። ስለ አፈጻጸሙም አቶ ሚሊዎን ነቅንቅ እንዳቀረቡት አዲሱ ፊደል ባዋጅ እንዲጸቅ የተደረገ እንደሆነ ጉዳዩ ጎላ ስለሚልና ስለሚከብድ አዲሱ ፊደል እስኪደራጅ ወደ አዲሱ እያደላን እንዲሰራ ብናደርግ ስራችን ይቃናል፡፤ የመኪና ጽህፈትም አቶ ዘውዴ ባቀረቡት አዲስ ፊደል ባለው መኪና ሊካሄድ ይችላል ብለው አበቁ። መ/ሀ/ወ/ቂ ደሞ ጉዳይ ባዋጅ ቢወጣ አልጠላም ግን ይውጣ ብዬ አልሞክርም ለመንግስት ጥቅም ሲባል ውስጥ ለውጥ ይራመድ በትዕዛዝ የሚሆን አይደለም ብለው አስረዱ።

አቶ ሰይፉ የሚቀጥሉትን አራት ሀሳቦች አቀረቡ

፩/ መጀመሪያ ከጥናቱና ካዲሱ ፊደል የትኛውን መያዝ እንደሚቻል መወሰንና ከዚህ በኋላ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ ጉዳዩን በማሰራጨት በዝግታ ማስማተና ጥቅሙን

መግለጥ

፪/ ይበልጥ ደሞ የፊደሎች መሻሻል የሚሰጠውን ጥቅም አጉልቶ ለህዝቡ ማሳወቅ

፫/ የፊደሉን ጥቅምና አላማ ህዝቡ እንዲያውቀው ተደርጎ መ/ቤቶችና ደራሲዎች በሁለቱም ፊደሎች እንዲሰሩ ማስደረግ ይሻላል።

፬/ ከዚህ በኋላ ሀሳቡ ከደገፈ የድሮው እየቀረ ሲሄድ ባዲሱ ብቻ ሊጠቀም ይችላል ብለው ዘርዝረው አቀረቡ።

ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ሚሊዎን ነቅንቅ ቀጥለው ሀሳቡ ሁሉቱን ፊደሎች ጎን ለጎን እንዲሰሩ ማድረግ ነው በኔ አስተያየት ግን የድሮው ፊደል የሚሰራበት ጊዜ እስካልተወሰነ ድረስ ብዙ ችግርና ድብልቅልቅ ይፈጥራል አዲሱን ፊደል ለመማር ጥቂት ደቂቃዎችን ቢወስድም ሰውን የለመድከውን ትተህ አዲሱን ልመድ ብንለው አዲሱን ትቶ የተለመደውን መርጦ ይገኛል። ለመማር ወይ አለመማር ለመቀበል ወይም አለመቀበል ሙሉ ፈቃድ ብንሰጠው የድሮውን ይመርጣል። አስፈላጊ የሚሆነው መጀመሪያ አዲሱን ማስተማርና በዚያው እንዲቀጥል ማድረግ ነው። የህግ ሰራው ማስገደድ ብቻ እንደሆነ መታሰብ የሉብትም ህግ አስተባባሪም ነው። ለምሳሌ የት/ሚር አዲሱን አጻጻፍ ለማስተማር በዙ ጊዜና ገንዘብ አጥፍቶ ህግ ያልተከተ እንደሆነ ጊዜውም ገንዘቡም ባክኖ መከረቱ ነው ብለው በማስረዳታቸው በስራ ላይ የማዋሉ ዘዴ ወደፊት ይታሰብበት ተብሎ ታለፈ።

አቶ አበበ ረታ የኢትዮጵያ ትምህርት ጠባቂ ቤተ ክህነት ነው ሲባል ከቤት ክህነት አንድ አባል እንዲገኝ የተባለው ሀሳብ ውሳኔ ስለአልተሰጠው ለዚህ ጉዳይ አባለነት ሊመረጥ የሚችሉ የታወቁ ሰዎች ተመርጠው የኮሚቴው አባል እንዲሆኑ መወሰንና መጠየቅ ያስፈልጋል ብለው ሀሳብ ሰጡ። አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ የኢትዮጵያ የትምህርት ጠባቂ ቤተ/ክህነት ነው መባሉን ተቃውመው ድሮ ትህምርት በቤተ ክህነት እጅ የነበረው ክርስትናን ለማስፋፋት ቁልፍ ስለነበረ ነው አሁን ግን ትምህርት ብዙ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ይዞ በመገኘቱ መንግስት ሀላፊነቱን ወስዶ ይሰራል። ቤተ ክህነት ለቋንቋ ጠባቂ ከሆነ ምናልባት ለግዕዝ ይሆናል። በቤተ ክህነት የሚማር አንድ ተማሪ ከፊደል ጀምሮ አቡጊዳንና ፊደለ ሐዋርያን ከጨረሰ በኋላ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈ ወንጌል ይገባል እንጂ አምርኛ የሚያስተምር ቤተ ክህነት ካለ አሁን የተጀመረ ነው። ፊደለ ሐዋሪያም ሆነ ወንጌል የተጻፉት በግዕዝ ቋንቋ ስለሆነ ትርጓሜን ለማያውቅ እጅግ ከባድ ነው። እንዲሁም ጸሎትም ሆነ ቅዳሴ የሚደረገው በግዕዝ ቋንቋ ነው። የአማርኛ ቋንቋ በሀገ መንስግስቱ የተሰጠን ብሔራዊ ቋንቋ ስለሆነ ያማርኛ ቋንቋ ጠባቂ መንግስት ነው። ከቤተ ክህነት አንድ ሰው ተጋብዞ ከኛ ጋር ቢያጠና ግን ደስተኛ ነኝ ብለው አበቁ። ብላታ መርሥዔ ቀጥለው መሰረቱ ያው ነው ምንም እንኳን ኮሚቴው በጽ/ሚር ቢታዘዝ ቤተ ክህነት የኮሚቴውን ሀሳብ እንዲያውቀውና እንዲረዳ አንድ ሰው ተውክሎ ከኛ ጋር ቢያጠና መልካም ነው አሉ።

በመጨረሻ የሚከለተው ውሳኔ ተደርሶ የመጀመሪያው ስብሰባ ተዘጋ። አባ ሀብተ ማሪያ ወርቅነህ[12] ወይም አባ ሳሙኤል ተረፈ በቤተ ክህነት ስም የኮሚቴው አባል እንዲሆኑ ብፁዕ አባታችን[13] እንዲጠየቁ። ከ አመት በፊት የተደረገው የፊደል ማሻሻያ ድርሰት ባቶ ሚሊዎን ነቅንቅ በኩል ከት/ሚር ወጥቶ ከሚመጣው ስብሰባ በፊት ለአባሎቹ እንዲታደል የሚል ነው።

ሁለተኛው ስብሰባ

በስበሰባው የተገኙ አቶ አበበ ረታ ሰብሳቢ

ብላታ ወ/ጊ/ወ/ዮሐንስ

አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ

አቶ ሰይፉ ፈለቀ

አቶ ሳሙኤል ተረፈ ከቤተ ክህነት ተወክለው መስከረም ቀን ዓ/ም ተጀመረ። ብላታ መ/ሀ/ወ/ቂ፣ ሀዲስ ዓለማየሁና ከበደ ሚካኤል በዚህ ስብሰባ አልተገኙም።

ስብሰባዊው አቶ አበበ ረታ ስብሰባውን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር አቶ አዲስ ዓለማየሁ የግርማዊነታቸው አምባሳደር ሆነው ወደ እንግሊዝ አገር ለመጓዝ ጊዜው በመቅረቡ ለመገኘት አለመቻላቸውን ግን ጉባኤው የተነጋገረበትን በሙሉ መደገፋቸውን ገልጸው ቀጥለው ከቤተ ክህነት አንድ ሰው ተወክሎ አብሮ እንዲያጠና ባላፈው ጉባኤ በተወሰነው መሰረት አቶ ሳሙ ኤል ተረፈ በጉባኤው መገኘት ጥናቱን የተሟላ እንደሚታደርገው ገልጸው ስብሰባውን ከፈቱ።

በመጀመሪያው ጉባኤ ባለፈው ተጥንቶ የነበረውን ማየት አስፈላቲነቱ ታምኖበት ተጠይቆ የነበረውን "ለወጣቶች ዕድል ከትምህርት ወዳጆች" የተባለውን አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሰረት ቀርቦ ለጉባኤው ተሳታፊዎች ታደለ።፡ ቀጥለው አቶ ሳሙኤል የፊደሉን መሻሻል በግላቸው የሚቃወሙ አለመሆናቸውን ግን ለውጡን ቤተ ክርስቲያን የማትፈግፍ መሆኗን የሚናገሩትም በቤተ ክህነት ስም ስለሆነ ለውጡን አለመደገፋቸውን ግን ጥናቱን ለማጥናትና ሀሳብ ለመካፈል መምጣታችውን አበሰሩ።

ሰብሳዊው ቀጥለው ፊደል እንዲለወጥ የሚፈልግ የለም የኛ ጥናት የአማርኛ ፊደል ሕግን እንዲጠብቅ ብቻ ነው በማለት ላቶ ሳሙኤል አስረድተው በዕለቱ መነታገሪያ የሆኑትን የሚከተሉትን ሶስት አርዕስቶች አቀረቡ።

ሀ/ ማንም የሚናገረውን ቋንቋ ባጭር ጊዜ አንባቢ እንዲሆን ፊደል ሕግን እንዲጠብቅ ማስማማት

ለ/ በመጽሐፉ ውስጥ ከተመለከቱት የፊደል መሻሻያ ሐሳቦች የሚስማማውን መምረጥ

ሐ/ በአደራረግና ባፈጻጸሙ የሚያስከትልውን አጥንቶ መወሰን ነው ብለው አስረዱ።

አቶ ሳሙኤል ተረፈ ራሳቸው በተመለከቱት መሰረት አማርኛን ህግ ማስጠበቅ እንጂ መለወጥ የማይቻል በመሆኑ ተስማሚ ነጥብ ከተገኘ በግላቸው መስማማታቸውን ከገለጡ በኋላ ከቤተ ክህነት በኩል ላለ ሀሳብ ግን ሀሳብ መስጠት አለመቻላቸውን ገለጹ። ፊደሉ ይሻሻል አይሻሻል የሚሉ እንደሆነ ከነምክንያቱ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አስጠንተው እንዲያቀርቡ በጉባ ኤው ተስማምተው መልሱ እስኪመጣ ስብሰባው ተቀጥሮ ጉባኤው ተዘጋ።፡

**ሶስተኛው ስብሰባ**

በዚህ ስብሰባ አቶ አበበ ረታ፣ አቶ ከበደ ሚካኤል፣ ብላታ መርሥኤ ሀዘንን፣ አቶ ሚሊዮን ነቅንቅን፣ አቶ ሰይፉ ፈለቀን፣ ብላታ ወልደ ጎርጊስን ይዘው ኅዳር ቀን ዓ/ም ስብሰባውን ቀጠሉ።

ሰብሳቢው አቶ አበበ ረታ የስብሰባውብ ምክንያት ፊደል ሥርዐት እንዲጠብቅ ለማድረግ የተጀመረውን ጥናት ለመቀጠልና ፍጻሜ ለማድረስ መሆኑን ገለጸው በሁለተኛው ስብሰባ የተደረሰባቸውን ውሳኔዎች አብራርተው ስብሰባውብን ከፈቱ እነሱም

፩/ የአማርኛ ፊደል ሕግ እንዲጠብቅ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ መስማማታቸውን

፪/ ቤተ ክህነት በራሱ በኩል ያለውን ተቃውሞ ወይም ድጋፍ ከነምክንያቱ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ ወኪላቸው ባሉበት መወሰኑን

፫/ በመጽሐፉ ውስጥ የፊደል ማሻሻል ሀሳቦች የሚስማማውን እንዲመርጥ ይህ ደሞ ውሳኔ እንደሚያስፈልገው

፬/ ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ዐይነት አኳኋን በሥራ ላይ እንደሚውል

ተወያትተን ውሳኔ እንዲሰጥበት።

በሁለተኛው ተራ ቁጥር በተመለከተ ከቤተ ክህነት ባስራ አምስት ቀን ውስጥ እንዲቀርብ የተባለው እንዳልደረሳቸው አሁንም እየተጠባበቁ እንደሆነ እና በሶስተኛው ተራ ቁጥር ስለተገለፀው ግን ምርጫው በሚደረግበት ጊዜ ፊደሎቹ የእገሌ መባላቸው ቀርቶ ዘመኑ ያስከተለው መሻሻል እየተባለ እንዲጠራ ሲሉ ለጉባኤው መምሪያ ስጥተው ጨረሱ።

ቀጥለው አቶ ከበደ ሚካኤል ቅጥሎቹ ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚደግፉ መሆናቸውን ገልፀው የፊደሎችን መሻሻል ሀሳቡን ባመነጨው ሰው ቢጠራ የትሻለ መሆኑን አሳሰቡ። ለጥቀው ብላታ መርሥዔ ኀ/ወ/ቂ ቤተ ክህነት በጉባኤው እንዲሳተፍ ባሳሰቡት መሰረት መስማማታችውንና ወኪላቸው ባስራ አምስት ቀን ውስጥ አስጠንቼ አመጣለሁ ያለውን እስከዚህ ስብሰባ ድረስ አለማምጣቱን አመለከቱ። ቤተ ክህነት ጉዳዩን ካወቀውና ተካፋይ ከሆነ ስብሰባው እንዲቀጥል ፍታደኝነቱን መግለጹ ነው በማለት አስረዱ። ጉባኤውም ይህን ስብበስባ በሚመለከት የጥሪ ወረቀት መላኩን አረጋገጠ።

ከዚህ በኋላ ጉባኤው ከግዕዝ ጀምሮ ስድስቱን አዕጹቅ[14] ፊደላት ምልክቶች ከዚህ በታች እንደተገለፀው እንዲሆን ወሰነ።

፩ኛ/ ግዕዝ እናት ፊደል በመሆኑና ምልክት ወይም አናባቢ ስለሌለው የቀድሞው መልኩ እንዳለ እንዲቆይ።

፪ኛ/ ካብዕ ከረ፣ ከወና፣ ከፈ በስተቀር ሁሉም ሕግ የሚጠብቅ ስለሆነ ሕገ ወጦቹ ሕግ እንዲጠብቁ ተደርጎ የካብዕ ምልክት በፊደሉ በስተቀኝ በመሀሉ ላይ እንዲውል

፫ኛ/ ሳልስ ከስድስቱ በስተቀር ማለት ሀ፣ መ፣ ረ፣ ወ፣ የ፣ እና ፈ በስተቀር ሁሉም ሕግ የሚጠብቅ ስለሆነ ስድስቱ በሳልስነታቸው ከሌሎቹ ጋር ሕግ እንዲጠብቁ ተደርጎ የሳልስ ምልክት በቀኝ ግርጌ እንዲውል

፬ኛ/ ራብዕ ብዙው ሕገ ወጥ ስለሆነ ከሰላሳ ሶስቱ ሀያ ሁለቱ በስተቀኝ እግረ ቁልቁል ውጭ ሰባቱ ግራ ዛቢያ አራቱ ቀኝ ዛቢያ ያላቸው በመሆኑ የራብዕ ምልክት ሁሉ እግረ

ቁልቁል ውጭ እንዳይሆን ከመስመር በታች የሚውል ፊደል ስለሌለ ታውቆ በቴክኒክ በኩልም አስቸጋሪነቱ ስለታወቀ የራብዕ ምልክት በቀኝ ወይም በግራ መዋሉ ሳይወሰን የሳድስ ምልክት በሚወሰንበት ጊዜ አብሮ እንዲወሰን በቀጠሮ አድረ።

፭ኛ/ ሐምስ ሕግና ስራት ጠባቂ በመሆኑ በቀኝ ግርጌ የቀለበት ምልክት ተደርጎበት እንደመልኩ እንዲቆይ ጉባኤው ተስማምቷል።

፮ኛ/ ሳድስ በጠቅላላው ሕገ ወጥነቱ ከአስራ አምስት ዐይነት ይበልጥ ድብልቅልቅ በመሆኑ ማለት ከሰላሳ ሶስቱ ሰባቱ የርክርክ ምልክት፣ አንድ በፊደሉ ግርጌ በስተግራ የቀለበት ምልክት፤ አንድ በፊደሉ ራስጌ የቀለበት ምልክት፤ አስራ አምስቱ በፊደሉ ቀኝ በስትራስጌ ወይም በስተግርጌ የመቀለስ ምልክት አላቸው። ከነዚህ ከአስራ አምስቱ ውስጥ በስተግርጌ ግራ ስያፍ እግር ያላቸው ወይም እናታቸው ላይ ቅብ ያላቸው ሲሆኑ ሰባቱ በቀኝ ግርጌ ርሳጌ ወይም መሐል ምልክት አላቸው። ሁለት ደሞ በግዕዙ ፊደል ላይ ቅን አንገት ያላቸው አሉ። ለዚህ ሕገ ወጥ ፊደል በግዕዙ ፊደል መሐል ላይ በስተግራ ምልክት ይዋል ተብሎ ሀሳብ በቀረበው መሰረት በቴክኒክ በኩል የሚያስቸግር ነገር እንዳለ ተብራርቶ ከራብዕ ምልክት ጋር አብሮ እንዲወሰን በቀጠሮ ታለፈ።

፯ኛ/ ሳብዕ በአምስት ዐይነት ሕገ ወጥ ነው ማለት ከሰላሳ ሶስቱ ፊደሎች ውስጥ አስራ አምስቱ ግራ እግራቸው አንካሳ ነው። አስሩ በቀኝ ራስጌ በኩል የቀለበት ምልክት ሲኖራችው ስድስቱ እግረ ጎታታ ናቸው። አንዱ በቀኝ ራስጌ ምልክት አለው (ዮ) ሌላው (ጎ) አናቱ ላይ ነው። ለዚህ ፊደል በቀኝ ራስጌ በኩል የቀለበት ምልክት ቢታከልበት ተስማሚ ነው በማለት ጉባኤው ተስማምቷል።

ከዚህ በኋላ የፊደሎቹ ዐይነቶች እና ምልክቶች በቴክኒክ በኩል የሚያመጣው ችግር እንዳለ ወይም እንደሌለ ተጠንቶ እንዲቀርብ አቶ ሰይፉ ፈለቀ እና አቶ ዘውዴ ገ/መድኀንን ጉባኤው ወክሎ በአስር ቀናት ውስጥ አጥንተው እንዲያቀርቡ ተወስኖ ሶስተኛው ጉባኤ ተዘጋ።

## አራተኛው ስብሰባ

አራተኛው ስብሰባ ጥር ፬ ቀን ዓ/ም ብላታ መርሥዔ ሀዘን፣ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አቶ ሚሊዮን ንቅንቅ፣ አቶ ሰይፉ ፈለቀና አቶ ዘውዴ ገ/መድህን ባሉበት ሰብሳቢው አቶ አበበ ረታ በሶስተኛው ስብሰባ አቶ ሰይፉ ፈለቀና አቶ ዘውዴ አጥንተው እንዲያቀርቡ በተባለው መሰረት አጥንተው ማቅረባቸው በመግለስ በጉባኤው ስም ምስጋና በማቅረብ አያያዘው የራብ ዕና የሳድስ ምልክቶች ላይ ውሳኔ እንዳልተሰጠ በማስገንዘብ ምልክቶቹ በቀኝ ወይም በግራ ይውል አይውል እንደሆነ ለቴክኒክም የተሻለው እንዲመረጥ ውይይቱ እንዲቀጥል ብለው ስብሰባውን ከፈቱ።

ብላታ መርስኤ የራብዕ ምልክት በስተቀኝ መሆን አለበት ራብዕ አፍ የሚያስከፍት ስለሆነ ምልክቱ ቅናት ቢሆን የሳድስ ምልክት ደሞ ድፋት ቢሆን ጥሩ ነው። ድፋት እና ቅናት የዜማ ምልክት ስለሆኑ ታሪክን የተከተለ ወግን የተቀበለ ነው። የፊደሎቹ ምልክቶች በግራ ላይ መዋላቸውን ግን አልደግፍም ብለው ሀሳባቸውን አቀረቡ። አቶ ሰይፉ ፈለቀ በበኩላቸው የራብዕ እና የሳድስ ምልክቶች በስተቀኝ የሆኑ እንደሆነ እንዳጠናነው በቴክኒክ በኩል ችግር ይፈጥራል። ምክንያቱም የካብዕ፣ የሳድስ፣ የሐምስ እና ሳብዕ የዋሉት በስተቀኝ ነው። የብላታ ሀሳብ ከዶ/ር ሉባክ ጋር የተቀራረበ ነው። የድፋት እና የቅናት ምልክቶች በዜማ የተለመዱም ቢሆኑ ፊደል ላይ ያልተለመዱ ናቸው። ከዚህ በፊት እንደቀረበው ፊደሎች የእገሌ ሳይባሉ ጊዜው የፈጠራቸው/የፈለጋቸው ሆነው የድሮውን ያማርኛ ወግና ጠባይ ያልለወጡ መሆን አለባቸው። የራብዕ ምልክት ከተለመደው መንገድ ወጥቶ የታሪኩን መንገድ ለቆ በስተቀኝ የዋለ እንደሆነ ለተማሪዎች ሊያቸግር ይችላል ብለው ሀሳባቸውን ሰጡ። አቶ ዘውዴ በበኩላቸው የራብዕ ምልክት አሰጣጥ በስተግራ ወይም በሰቀኝ እንዲሆን በሚለው ስምምነት ከጠፋ በድምፅ ብልጫ ይወሰን አሉ። ሰብሳቢው ደሞ ጥናቱ በሁለት ይከፈላል ይኼውም አንደኛው የራብዕና የሳብዕ ፊደሎች ምልክቶች በቀኝ ወይም በግራ ይሁኑ የሚለው እና የጥንቱን በመከተል የፊደሉ ቅርጽ መልኩን ሳይለውጥ እንዲቆይ ምልክቱ ግን ለሁሉም አንድ እንዲሆን የሚለው ነው እንነጋገርበትና በድምጽ ብልጫ ብንወስን ይሻላል አሉ። አቶ ሰይፉ ቀጥለው የፊደሉ ቅርጽ የጥንቱን መልክ ሳይለቅ ከድሮው ወደ አዲሱ ለማስጠናት እዲቀና ወይም እንዲቀል ጥንትም ሲጻፍ ከግራ ወደ ቀኝ ስለሆነ ከግራ በኩል እየቀጠሉ መሄድ ይሻላል አሉ። አያይዘውም በተለይ እነ ተ ሲጻፉ ቅጥሉ በግራም በቀኝም ሲሆን አጻጻፉ በግራ መጀመሩ ለዚህ አስረጅ ነው። ለማተሚያ ስራ በቴክኒክ በኩል በግራ ወይም በቀኝ ይሁን ለማለት ከተደረገው ጥናት የበለጠ ሙከራ ተደርጎ ጉዳቱና ጥቅሙ ከታየ በኋላ ቢወሰን ይሻላል። አለያ ምልክቶች በቀኝ በኩል ይሁን ተብሎ አሰቀሞ ከተወሰነ በኋላ ችግር እንዳይፈጥር ጥናቱ ቢቀድም ይሻላል አሉ።

ከዚህ በመቀጠል ጉዳዩን አባሎቹ በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ከብላታ መርስኤ በስተቀር ሌሎቹ አቶ ሰይፉ ያቀረቡትን ሀሳብ ደግፈው የራብዕና የሳድስ ምልክቶች በግራ እንዲሆኑ ተስማምተው ምልክቱ ከቀኝ ይሁን ቢባል ባቀማመጣቸው ሁኔታ በቴክኒክ በኩል ታይቶ ጥቅምና ጉዳቱ እንዲታወቅ እንዲወሰን ተደረገ። ጥናቱ ካለቀ በኋላ የጉባኤው ሐሳብና አስተያየት ለግርማዊነታቸው ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተወስኖ ስብሰባው ተዘጋ።

## አምስተኛው ስብሰባ

በዚህ ስብሰባ በላታ መርሥኤ፣ ብላታ ወልደ ጊዮርጊዝ እና አቶ ከበደ ሚካኤል አልተገኙም። ሰብሳቢው አቶ አበበ ረታ፣ አቶ ሚሊዮን ነቅንቅን፣ አቶ ሰይፉን፣ አቶ ዘውዴን ይዘው ባራተኛው ስብሰባ ጉባኤው የደረሰበትን ጥናት ባጭሩ ገልጸው ፊደሎቹ መሰረታዊ መልካቸውን እንደያዙ ምልክቶቹ በቀኝ ወይም በግራ ቢውሉ ባሰራር ምን እንደሚያስከትል በቴክኒክ በኩል ያለው ሁኔታ ይሞከር የተባለውን አስታውሰው ስብሰባውን ከፈቱ።

አቶ ሰይፉ ፊደሎች ሕግ እንዲጠብቁ ውሳኔ መደረጉንና ሙከራውም ውሳኔውን እንደማይለውጠው አስረድተው በቴክኒክ በኩል ተሞክሮ ምን ዐይነት መልክና አሰራር እንደሚያስከትል ለማወቅና ፊደሎቹም ሕግን እንዲጠብቁ ከዚህ በፊት በተደረገው ጥናት ትልቅ ለውጥ ማምጣቱንና መሰረቱን ሳይለቅ በቀላሉ ለመታወቅ፣ ለማስተማርና ለመማር ምቹ እንደሆነ ገለጹ። ሰብሳቢው አያይዘው ውሳኔው ማለቁን የምልክቶቹ

አቀማመጥ በቴክኒክ በኩል ይሞከር የተባለው በመኪና ላይ የተወሰነው ምልክት ተቀርጾ በየፊደሉ ላይ ተሙቶ የሚያስከትለው ምልክት እንዳለ ለማየት እንዲረዳ ይሞከር የተባለው የምልክቶቹን ሁኔታ ለማረጋገጥ ወደፊት አንድ ስብሰባ ተደርጎ ያ ከታዩ በኋላ ለግርማዊነታቸው እንዲቀርብ ነው የተወሰነው ብለው ተናገሩ። ቀጥለው አቶ ሰይፉ በንግድ ት/ቤት ያማርኛን መኪናዎች የሚጠግንና የሚሰራ በዚህ ሙያው በጣም የታወቀ ሰው አለ። ይህን ሰው ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ አነጋግረነው ስለምልክቶቹ አሰጣጥ እኛ የመረጥነውን መሰረት አድርቶ የመኪናውን ፊደሎች እየለዋወጠ ሞክሮ ጉባኤው የተስማማበትን የተሻለ መሆኑን እና ከዚህ የተሻለ አለመኖሩን ገልጿል። እኔም አይቼ ሌላ የተሻለ አለመኖሩን አምኛለሁ በማለት ካብራሩ በኋላ ከዚህ ሰውዬ የበለጠ ከተገኘ እንደገና ይሞከር ካልተገኘ ግን በዚሁ ብንጸና ይሻላል አሉ።

ሰብሳቢው ሃሳቡን ለማጠቃለል በመኪና ሙከራ ተደርጎ የተሻለ መሆኑን ሌላ የተሻለ የቴክኒክ አዋቂ ከተገኘ በማናቸውም ጊዜ መሞከር የሚከለክል ነገር እንደሌለ አብራሩ። ስለምልክት አሰጣጥ ብዙ ሙከራ መደረጉን እና የተባለውም ባለ ሙያ በዚህ ዕውቀቱ የበሰለ ስለሆነ ሌላ ሙከራ እንደማያስፈልግ ባቀረቡት ሀሳብ ጉባኤው በዚህ ተስማማ። አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ለጥቀው አቶ ሰይፉ ያስረዱትን በማስታወስ የራብዕና የሳድስ ምልክቶች መሰረታቸውን ሳይለቁ እንደድሮው በግራ በኩል ባንድ ዓይነት እንዲሁኑ ሰለተስማማን ይህንኑ ማስታወስ ይጠቅማል በማለት ተናገሩ። የግዕዝ ቋንቋ ጥንታዊውን ሥርዓትና ያጻጻፍ ልምድ እንደ ጥንቱ ይዞ እንዲቀር ሁሉም በመስማማት አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ ቃለ ጉባኤውንና የጥናቱን መሰረተ ሀሳብ በራፓር መልክ አሰናድተው ለጉባኤው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ፈቃደኝነታቸውን ገልጸው ስብሰባው በዚሁ ተዘግቷል።

**ጉባኤው ከዚህ በታች የተዘረዘረውን ተስማምቶ ወስኗል**

፩/ ግዕዝ የተባሉት ዘይብሎች ማለት ሀ፣ ለ፤ ሐ፣ መ፣ ረ፣ ሰ፣ ሸ፣ ቀ፣ በ፣ ተ፣ ቸ፣ ነ፣ ኘ፣ ከ፣ ወ.]፣ ለ፣ ዘ፣ ዠ፣ የ፣ ደ፣ ጀ፣ ገ፣ ጠ፣ ጨ፣ ጰ፣ ፀ፣ ጸ፣ ፈ፣ እና ፐ የአማርኛ እናት ፊደሎች ስለሆኑ መልካቸው ሳይለወጥ መሰረተ ፊደል ሆነው እንዲቆዩ።

፪/ ካብዕ የሚለየው በግዕዙ ዘይብል ላይ አናባቢ ምልክት በመጨመሩ እንደ ሁ እንደ ቡ እንደ ሙ አናባቢ ምልክት በፊደሉ በስተግራ መሐል ላይ የጭረት ምልክት እንዲደርግበት።

፫/ ሳልስም የሚለየው በግዕዝ ዘይብል ላይ አናባቢ ምልክት በመጨመሩ ስለሆነ እንደ ሊ እንደ ታ እና እንደ ቢ ሁሉ ያናባቢው ምልክት በፊደሉ በስተግራ ግርጌ ላይ የጭረት ምልክት እንዲኖረው።

፬/ ራብዕም መለያው ያው በግዕዝ ዘይብል ላይ አናባቢ በመጨመሩ ነው። እንደ ታ እንደ ቃ እንደ ያ አናባቢው በስተቀኝ ግርጌ ላይ የጭረት ምልክት እንዲኖረው።

፭/ ሐምስም በግዕዙ ላይ አናባቢ በመጨመሩ ስለሆነ እንደ ሌ እንደ ሴ እንደ ቴ በፊደሉ በስትግራ የቀለበት ምልክት እንዲጨመርበት።

፮/ ሳድስም መለያው በዘይብሉ ላይ ምልክት መጨመሩ ስለሆነ እንደ ብ በፊደሉ በስተቅኝ ራስጌ አቅራቢያ የጭረት ምልክት እንዲኖረው።

፯/ ሳብዕም በግዕዙ ዘይብል ላይ ምልክት መጨመሩ ስለሆነ እንደ ሆ እንደ ሎ በፊደሉ በስተግራ ራስጌ የቀለበት ምልክት እንዲኖረው።

ከዚህ በተረፈ በስድስቱ ዘይብሎች ሐ፣ ሠ፣ ኀ፣ ኸ፣ ዐ፣ ና ጸ መልካቸው እንጂ በድምጻቸው ተመሳሳይ ወይም ጓደኛ ስላሏቸው ለግዕዝ እንጂ ላምርኛ ስለማያስፈልጉ ሕግ በጠበቀው ያማርኛ ፊደል ውስጥ እንዳይገቡ ተወስኗል። የሀያ ሰባቱ ዘይብሎችና የስድስቱ መደቦች ድምጽና አነባብ ከተለመደው ድምጽ የተለየ እንዳይሆን ተወስኗል።

ፈንጽቅ ፊደላት የሚባሉት ማለት ኰ፣ ጐ፣ ቋ፣ እና ኍ ባምስት መደብ የሚነገሩት ወገናቸው ከሆኑት በ ገ፣ ቀ፣ ሀ፣ ላይ ወ አጋዥ እየሆነ ቋራ የሚለው ቅዋራ ቋት የሚለው ቅዋት እየተባለ እንዲገባ ተወስኗል።

ሌሎቹ ዘመን አመጣሽ የተባሉት በግዕዙ ወይም በራብዑ ላይ የጫማ ወይም የባርኔጣ ምልክት እየተጨመረ የገቡ ፊደላት ማለት እንደ ሧ፣ እንደ ሏ፣ እንደ ሯ እና እንደ ፏ ያሉት ድምጽ ለዋጮች በሳድሱ ፊደል እና በዋ ራብዕ እየተጋገዙ ሊነገሩ ስለሚችሉ ለምሳሌ ሧርት ለሚለው ምዋርት፤ ፏፏቴ ለሚለው ፍዋፍዋቴ እየተባለ እንዲጻፍ ተሰውኗል።

ይህ ከላይ በኮሚቴው የተወሰነው ያማርኛ ፊደል ሕግን እንዲጠብቅ ከደረገ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሞች እንደሚሰጥ ኮሚቴው አስገንቦ አልፏል።

፩/ ያማርኛ ፊደል ከነጓዙና ከናበጋዙ ማለት ሰላሳ አራቱ ዘይብሎች(ግዕዝ ግዕዙ) በሰባት መደብ ሲዘረዘሩ በድምር ሲሆን አራቱ ፍንጽቅ ፊደላት በአምስት መደብ ሲዘረዘሩ ደሞ ፳ ናቸው። በግዕዙ ወይም በራብዕ ላይ የመጫሚያ ወይም የባርኔጣ ምልክት እየተጨመረ የሚጻፉ ብዛታቸው ከ የማያንሱ አብረው ተደምረው ያማርኛ ፊደል ጠቅላላ ድምሩ ነው። ነገር ግን ኮሚቴው ባጸደቀው ሕግ የጠበቀው ፊደል ግን ዘይብሎችና ፬ ያናባቢ ምልክቶች ተደምሮ ጠቅላላ ብቻ ነው።

፪/ በዚህ ዐይነት በጊዜ ቁጠባ በኩል ፊደልን ለመማር ዘጠኝ ወር የሚወስድበትን ሰው አንድ ወር፤ ዘጠኝ ቀን የሚወስድበትን ሰው አንድ ቀን፤ ዘጠኝ ሰአት የሚወስድበትን ሰው አንድ ሰዓት ብቻ በመውሰድ የጊዜውን ስምንት እጅ ወይም የጊዜውን በመቶ ይቆጥባል።

፫/ በቴክኒክ ቅልጥፍና በኩል ሕግ የተከተለውን ፊደል ብንጠቀም እንደሌሎቹ ፊደሎች ያማርኛ የጽሕፈት መኪና በቅልጥፍና እንዲሰራ መንገድ ይከፍታል።

፬/ በማተሚያ ቤት የፊደል መልቀም ስራ የሚወስደውን ጊዜና የመኪና ጽሕፈት ለመማር የሚወስደው ጊዜ እንዲሁም ያማርኛን ፊደል የሚቀርጸው ፋብሪካ የሥራ ጊዜ በመቶ ያቃልለዋል። ይህ በበኩሉ የትምህርት ስራ እንዲቀላጠፍ መንገድ ይጠርጋል።

፭/ አማርኛን ለመጻፍ የስህተት ምክንያት የሆኑት ፊደሎች ሲወገዱ ስህተቱም አብሮ ስለሚጥፋ አማርና ለራሱ የሚያስፈልጉትን ይዞ ግዕዝ ያልተማሩትን ያማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ባማርኛ ዛሬ ድምጻቸው አንድ ዐይነት የሆኑት ፊደላት እነ ሀ፣ ሐ፣ ሃ፣ ኀ፣ ሓ፣ ኋ፣ ሠ፣ ሰ፣ ጸ፣ ፀ፣ አ፣ ኣ፣ ዓ፣ ዐ፣ ኸ፣ በአግባቡ እየለዋወጠና እየደባለቀ ለመጠቀም ከማስቻሉም በላይ ተማሪውንም አስተማሪውንም ከብዙ ልፋት ስለሚያድን ይህ ራሱ አንድ ትልቅ መሻሻል ነው።

፮/ የቢሮ ሥራ ጊዜን በመቆጠብ ፊደላችን ሕግ ሲጠብቅ ዛሬ ፊደሎችን ለማግኘት፣ ለማስቀመጥና ለመለየት ከመዝገበ ቃላት አንድ ቃል ለመመልከት፣ የልክ ቁጥር ለማግኘት ፊደሎች በዝተው ጊዜ ስለሚወስድ የሚጠፋውን ጊዜ በመቶ ስለሚቆጥብ በቅልጥፍና ረገድ ጥቅሙ እጅግ ብዙ ነው።

፯/ በገንዘብ ቁጠባም በኩል እጅግ ብዙ ማትረፍ እንዲሚቻል ተማሪዎችን ለማሰልጠን ወይም የመኪና ጽሕፈት ለማስተማር ከተመደበው ጊዜ በመቶ ተቆጥቦ በመቶውን ጊዜ ብቻ ትምህርቱ ሊሰጥ ይችላል። በደመወዝም በኩል ላስተማሪ የሚወጣውን በመቶ ይቆጠባል ወይም በዚያው በተመደውም ገንዘብ ዘጠኝ ጊዜ የበዙ ተማሪዎች ማስተማር ይችላል።

፰/ በብሔራዊ ጥቅም በኩል ዛሬ በኢትዮጵያችን[1] ባምስትና ባስራአራት ዓመት ዕድሜ መካከል ያለው ሕዝብ እስከ አምስት ሚሊዮን ሲገመት የትምህርት ዕድል ያገኙት ፳ በመቶ ብቻ መሆኑ፤ በአስራ ስምንትና በአርባ አመት መካከል ወደ አስር ሚሊዮን ከሚሆኑት መጻፍና ማንበብ የማችሉት ከ፳እስከ ፴ በመቶ መሆናቸው ሲገመት የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት፣ የመንግስት ሕግና ማስታወቂያ እንደዚሁም ልዩ ልዩ ጽሑፎች የሚታተሙበትን ፍርድና ፍትሕ የሚሰጥበትን በሔራዊ ማስታወቂያና መተያያ የሆነውን ይህን ያማርኛ ቋንቋ ለሁሉም ለማዳረስ እንዲመችና ወደፊትም ከፋ ያለ ጥቅም ሰለሚያስገኝ በተጠናው መሰረት ፊደላቱ ሕግ መጠበቁ ስለማይቀር መጻሕፍትና ጽሑፎች በብዛት በድሮው ዘዴ ከመታተማቸው በፊት በዚህ ባዲሱ ሕግን በጠበቀው ፊደል እንዲታተሙ ለማድረግ ባስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ አድፈላጊ መሆኑን።

፱/ በሰነ መንግስት በኩል ያፍሪቃ አገሮች ያፍሪቃ የሆነውን የሚወዱበት የውጭ የሆነውን የሚጠሉበት ጊዜ

ላይ ስለአሉ ፊደላችን ሕግ ከጠበቀ ሌሎች ያፊሪቃ አገሮች ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ቋንቋችን ዘመድና ወዳጅ ሊያፈራልን ይችላል።

፲/ ባስተሳሰብ፣ በአጻጻፍ፣ ባስተያየትና በምርምር የተፋጠነ እርምጃ በማድረግ ዕድገትና ፍጥነት እንደ ሀይማኖት ሆነው በሚገሙቱበት በ፳ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ ለፊደል ጥናት የሚጠፋውን ጊዜ በመቶ መቀነስ ራሱ በታሪክ መዝገብ ላይ ክብርና ሞገስ ተጎናጽፎ ለዘላለም መኖር ነው።

**ክንፈ ሚካኤል**

ከኖርን ለኢትዮጵያ እንኑር አቦ

ሚያዝያ ፪ ፳፻፩ ዓ/ም

ሜልበርን፣ ኽታች ኽስር

**ዋቤዎች**


፩ /ጸሀፊው አይታወቅም፣ ፲፱፻፹፪፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርመራ መጽሔት ቅጽ 8 ቁ፤ 1 የአማርኛ ፊደል ሕግን እንዲጠብቅ ለማድረግ የተዘጋጀ ራፓር ማስታወሻ ገጽ -

፻፵፬።

፪ / አብርሃም ደሞዝ፣ 1983፣ Ehtiopian Studeies Amharic Script Reform Reports pp.393-411.

፫ / ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ዓ/ም መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ። ደስታ ተ/ወልድ አሳታሚ።

ዓ/ም መዝገበ ፊደል የግዕዝና ያማርና ቋንቋ መክፈቻ ቅዱስ አላዛር ማ/ቤት ድሬዳዋ።

ዓ/ም አበገደ ፊደልና ፊደልዋሪያ የልጆች አፍ መፍቻ፣ ቅዱስ አላዛር ማ/ቤት ድሬ ዳዋ።

ደስታ ተከለ ወልድ፣ ፲፱፻፳፰፣ ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ ዐጭር ያማርኛ ግስና ርባታ ከነፊደሎቹ፣ ቅዱስ አላዛር ማ/ቤት ድሬ ዳዋ።

፲፱፻፵፯፣ ግዕዝ መሠረተ ትምህርት ርባሐ ስም ወአንቀጽ የስምና የአንቀጽ ርባታ፣ አርቲስቲክ ማ/ቤት አ/አ።

መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ፲፱፻፺፱፣ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት አ/አ ዩኒበርሲቲ ማተሚያ ቤት ፣ አዘጋጅ ልጃቸው አምኃ መርስኤ።